**አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.)**

**Lion Insurance Company (S.C)**

# የዳይሬክተሮች ቦርድ
# የ2015 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. የ2022/23)
# የስራ አፈፃፀም ዓመታዊ
# ሪፖርት



**ታህሳስ 20/2016 ዓ.ም**

# የአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.)
# የ2015ዓ.ም በጀት አመት (2022/23)
# የዳይሬክተሮች ቦርድ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት

**የተከበራችሁ ውድ ባለአክሲዮኖች፣የኩባንያችን ማኔጅመንትና ሠራተኞች፣ የኩባንያችን የውጭ ኦዲተሮች ተወካይ፣ እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው መ/ቤቶች ተወካዮች፣ ክቡራትና ክቡራን፣**

በቅድሚያ፤ እንኳን ለአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.) 16ኛ መደበኛ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሰላም መጣችሁ እያልኩ፣ የኩባንያውን ዓመታዊ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት በዚህ ጉባኤ ላይ ሳቀርብ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል፡፡ ሪፖርቱ በዋናነት በበጀት ዓመቱ የሥራ አፈፃፀም፤ ባጋጠሙ ችግሮችና በተወሰዱ መፍትሔዎች፤ እንዲሁም በቀጣይ መከናወን ባለባቸው ዋና ዋና ተግባራት ላይ ያተኩራል፡፡

## 1. የመድን ኢንዱስትሪው አጠቃላይ ሁኔታ፣

የመድን ኢንዱስትሪው፣ የተለያዩ ተግዳሮቶች የተጋረጡበት ቢሆንም፣ በበጀት ዓመቱ በኢንዱስትሪ ደረጃ ብር 22.9 ቢሊዮን አረቦን የተሰበሰበ ሲሆን፤ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር፤ የ37.5 በመቶ ብልጫ ሊያሳይ ችሏል፡፡ የአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ ድርሻም ከገበያው ብር 827.4 ሚሊዮን ሆኗል፡፡

## 2. የኩባንያችን እቅድ አፈጻጸም፣

እንደሚታወቀው፤ ባለፈው በጀት ዓመት በሀገራችን የተወሰኑ አካባቢዎች በተከሰተት ያስመረጋጋት ሁኔታዎች የተነሳ የኢኮኖሚው መቀዛቀዝ የተስተዋለ ቢሆንም፤ኩባንያችን በበጀት ዓመቱ ያሳየው የሥራ እንቅስቃሴና የተገኘው ውጤት በታቀደው መሠረት የተከናወነና አበረታች ነበር፡፡

### 2.1. ሃብት እና ዕዳ፣

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የኩባንያው አጠቃላይ ሃብት ብር 2 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን፤ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃጸር የብር 754.2 ሚሊዮን ወይም የ46.9 በመቶ እድገት አስመዝግቧል፡፡ ይህ የሚያሳየው ኩባንያችን በጠንካራ መሠረት ላይ እንደሚገኝና የጠለፋ ዋስትና ሰጪ ድርጅቶችን ጨምሮ በባለ ድርሻ አካላት ዘንድ ጥሩ የገበያ ተቀባይነት እንዳለው ነው፡፡

በሌላ በኩል የኩባንያችንን ዕዳ ስንመለከት በበጀት ዓመቱ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር የብር 678.4 ሚሊዮን ወይም የ68.5 በመቶ ብልጫ በማሳየት ብር 1.6 ቢሊዮን ሲደርስ

ችሏል፡፡ ለዚሁ ጭማሪ አስተዋፅኦ ካደረጉት ምክንያቶች በዋናነት የመጠባበቂያ ሂሳብ መጨመሩ ነው፡፡

## 2.2.የአረቦን ገቢና ስብጥር፣

በተጠናቀቀው በጀት አመት ኩባንያችን በጠቅላላ መድን እና በህይወት የመድን ዋስትና ዘርፎች አጠቃላይ የአረቦን ገቢ ብር 827.4 ሚሊዮን ያስመዘገበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥም ብር 4.4 ሚሊዮን የተገኘው የካቲት 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ከተደረገው የህይወት መድን ዋስትና ዘርፍ ነው፡፡ ይህ አጠቃላይ ውጤት ባለፈው ዓመት ከተመዘገበው ብር 464 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር ብር 363.4 ሚሊዮን ወይም 78.3 በመቶ ብልጫ ያለው ሲሆን፤ የጠቅላላ መድን ዘርፉን ብቻ ስናነፃፅር ከብር 464 ሚሊዮን ወደ ብር 823 ሚሊዮን በማደግ የብር 359 ሚሊዮን ወይም 77.4 በመቶ እድገት አስመዝግብ ከፍተኛ የሆነ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህም ኩባንያው በገበያው ያለውን ተወዳዳሪነትያመላክታል፡፡

የኩባንያችን የዋስትና ዓይነቶች ስብጥር ሲታይ ከአጠቃላዩ የጠቅላላ መድን ዋስትና አረቦን ገቢ፤ 69.2 በመቶው የተሽከርካሪ መድን ዋስትና ድርሻ ሲሆን፣ ቀሪው 30.8 በመቶ ደግሞ ሞተር-ነክ ካልሆኑት የዋስትና ዓይነቶች የተሰበሰበ ነው፡፡ ከዚሁም ገንዘብ-ነክ እና የኃላፊነት መድን ዋስትናዎች በቅደም ተከተል 8.1 በመቶ እና 8.8 በመቶ ድርሻ ሲይዙ ችለዋል፡፡

## 2.3.የካሳ ክፍያ አፈጻጸም፣

በበጀት አመቱ የተፈፀመው አጠቃላይ የካሣ ክፍያ ወጪ፣ብር 292.8 ሚሊዮን ሲሆን፣ከዚህ ውጪ፣ በእንጥልጥል ላይ ላሉና ላልተመዘገቡ የካሣ ጥያቄዎች ክፍያ መጠባበቂያ የሚሆን፣ በድምሩ ብር 239.7 ሚሊዮን፣ ወደ 2016 ዓ.ም በጀት ዓመት ተሳልፏል፡፡

## 2.4. የውል ሥራ ውጤት፣

ኩባንያው በበጀት ዓመቱ፣ ከውል ሥራ የመነጨ ብር 153.8 ሚሊዮን ትርፍ ማግኘት የቻለ ሲሆን፣ ይህም ካለፈው ዓመት ውጤት ጋር ሲነጻጸር፣ የብር 8.5 ሚሊዮን ወይም የ5.9 በመቶ እድገት አሳይቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ፣ በሁሉም የዋስትና ዘርፎች የተሻለ አፈፃፀም ታይቷል፡፡

የኩባንያችን ጥቅል የካሣ ምጣኔ (ማለትም:- Loss-Ratio)፤ 64.8 በመቶ የደረሰ ሲሆን፣ ይህም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 70 በመቶ ጣሪያ ጋር ሲነጻጸር፣ የተሻለ የካሳ አፈጻጸም የታየበት ሁኔታ ነበር፡፡

## 2.5. ከልዩ ልዩ ምንጭ የተገኘ ገቢ፣

የኩባንያው የካፒታል አቅም ውሱን መሆኑ ከኢንቨስትመንት የሚገኘው ገቢን ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ቢያሳድርም፤ ቦርዱ እና ማኔጅመንቱ ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት በበጀት አመቱ ከተቀማጭ ገንዘብ

ወለድ፣ ከተለያዩ ኩባንያዎች የተገኘ የትርፍ ክፍፍል፣ እንዲሁም ከህንጻው ኪራይ፣ በጥቅሉ ብር 95.7 ሚሊዮን ማግኘት ተችሏል፡፡ የተጠቀሰው ገቢ ከቀደመው ዓመት ጋር ሲነጻጸርም፣ የብር 21.4 ሚሊዮን ወይም የ29 በመቶ ብልጫ አሳይቷል፡፡

## 2.6. አስተዳደራዊና አጠቃላይ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች፣

ለአስተዳደራዊና ለሥራ ማስኬጃ የወጣው ወጪ ብር 173.9 ሚሊዮን ሲሆን፤ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የብር 18.3 ሚሊዮን ወይም 11.7 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህም የሆነው የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም፣ የህንጻ እርጅና ተቀናናሽ እና ሌሎች የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ጭማሪ በማስመዝገባቸው ነው፡፡

## 2.7. ትርፍ፣

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ኩባንያችን፣ ከግብር በፊት ብር 75.6 ሚሊዮን ያልተጣራ ትርፍ ያገኘ ሲሆን፣ ይህም ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነፃጸር የ11.7 ሚሊዮን ወይም የ18.3 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ግብር፤ ህጋዊ መጠባበቂያ፤ ክፍያ ተቀንሶ የተገኘው የተጣራ ትርፍ ፣ብር 70.6 ሚሊዮን ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው የአንድ አክሲዮን አማካይ ትርፍ ድርሻ /Earning Per Share/ 31.3 በመቶ ነው፡፡

## 2.8. የሰው ኃይል አስተዳደር

በበጀት ዓመቱ ማጠናቀቂያ ላይ፣ የኩባንያው ሠራተኞች ብዛት 336 ሲሆን፣ ከዚህ አጠቃላይ ብዛት ውስጥ 178 (53 በመቶ) ሴቶች ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ 158 (47 በመቶ) ደግሞ ወንድ ሰራተኞች ናቸው፡፡ ኩባንያው በበጀት ዓመቱ ውጤት ተኮር የምዘና ስርዓት (ባላንስድ ስኮርድ ካርድ (BSC) ተግባራዊ በማድረጉ የሰራተኞችን ምርታመነት በማሳደግ ባለው የሰው ሀይል የተሻለ የስራ አፈፃፀም ሲያስመዘግብ ችሏል፡፡ የኩባንያውን የሰው ኃይል አቅም ለማጎልበት፣ በተለያዩ መስኮች ለሰራተኞች የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

## ውድ ባለአክስዮኖች፣

ይህ ከፍ ሲል የተገለፀው ውጤት፣ ካሉብን ውስንነቶችና ውጫዊ ተግዳሮቶች አኳያ ሲመዘን፣ እጅግ አበረታች ነው ማለት ይቻላል፡፡

# 3. ያጋጠሙ ተግዳራቶችና ውስንነቶች እንዲሁም የተወሰዱ መፍትሔዎች፣

## 3.1. ያጋጠሙ ተግዳራቶችና ውስንነቶች፣

- በሀገራችን በተወሰኑ አካባቢዎች እየታየ ባለው የፀጥታ መደፍረስ ምክንያት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ ሲቀዛቀዝ ችሏል፤ እንዲሁም በሽያጭ እና በካሣ ክፍያ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፤

• በኮንስትራሽን ዘርፉ ትልልቅ ስራ-ተቋራጮች ጭምር ኪሳራ ያጋጠማቸው በመሆኑ፤ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸው የተለያዩ የዋስትና (ቦንድ) ካሣ ጥያቄዎች የቀረበበት አጋጣሚ ተፈጥሯል፡፡

• የተሽከርካሪዎች አደጋ እየተባባሰ መምጣቱ፣ እንዲሁም በሀገሪቱ ባጋጠመው የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና ዋጋ ግሽበት ምክንያት የመለዋወጫ ዕቃ ዋጋ መወደድ እና የጥገና ዋጋ መጨመር በካሣ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል፤ ከዚህ በተጨማሪ የዋጋ ግሽበቱ የኩባንያው ልዩ ልዩ የአስተዳደራዊ ወጪዎች እንዲንሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

• በኢንሹራንስ ዘርፉ በቂ የሆነ የሰለጠነ የሰው ሀይል ባለመኖሩ ምክንያት የሰለጠነ የሰው ኃይልን የተሻለ ጥቅማ ጥቅም እና ደመወዝ በመስጠት መነጣጣቅ መቀጠሉ የተረጋጋ የሰው ኃይል እንዳይኖር በማድረግ ጫና ማሳደሩ ዋና ዋናዎቹ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

## 3.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች/የተከናወኑ ስራዎች/፣

➢ የአደጋ ስጋት (ሪስክ) አስተዳደርን በማጎልበት የኩባንያው ላይ የተጋረጠውን የአደጋ ስጋት በመለየት፣ ኩባንያው መውሰድ ያለበትን ስጋቶች መጠን (Tolerance Limit) በማበጀት እና አደጋውን ገምግሞ አደጋ ሲቀንሱ የሚችሉ ስራዎችን አስቀድሞ በመስራት የኩባያውን አሰራር ጤናማና ውጤታማ ለማድረግ በብሔራዊ ባንክና በኩባንያችን ፖሊሲ እና መመሪያ መስፈርት መሠረት የዳይሬክቶሮች ቦርድ ከፍተኛ ስራ ሰርቷል፡፡

➢ በሀገራችን በተወሰኑ አካባቢዎች በተከሰተው የፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት የተከሰቱ ተግዳሮችን በመመከት በበጀት አመቱ ታቅዶ የነበረውን ገብ ለመምታት የዳይሬክተሮች ቦርድ ከማኔጅመንቱ ጋር በቅርበት በመስራትና ከፍተኛ አመራር በመስጠት ይህ አመርቂ ውጤት ሊመዘገብ ችሏል፡፡

➢ በበጀት ዓመቱ የስትራቴጂክ ማኔጅመንት መተግበሪያ መንገዶች አንዱ የሆነውን ውጤት ተኮር የምዘና ስርዓት (ባላንስድ ስኮርድ ካርድ (BSC) ተግባራዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡

➢ የሕይወት መድን ሽፋን ስራን የካቲት 2015 ዓ.ም በመጀመር እስከ የበጅት አመቱ ማብቂያ ድረስ ብር 4.4. ሚሊዮን ለመሰብሰብ ተችሏል፤ በቀጣይም የሕይወት መድን ሽፋን ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ለመስራትና በዘርፉም አመርቂ ውጤት ለማምጣት ታቅዷል፡፡

➢ የመልካም አስተዳደር አሰራርን ማጎልበት፣ከተለያዩ አጋር ኩባንያዎች ጋር ያለንን የስራ ግንኙነት ማጠናከር፣ አዳዲስ ደንበኞችን ማፍራትና ያሉንን ደንበኞች በትጋት በማገልገል ግንኙነታችን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡

## 4. የትኩረት አቅጣጫዎች፣

### 4.1. የሰው ኃይል ልማት፣

- የሠራተኞችን ሙያዊ አቅም ለመገንባትና የኩባንያችንን ተወዳዳሪነት የበለጠ እንዲያጎለብት ለማስቻል፣ እንዲሁም ተተኪ አመራሮችን ለማፍራት ሥልጠና ላይ በስፋት ይሠራል፡፡

### 4.2. ኦኘሬሽን፣

በቀጣዩ (ማለትም፡-በያዝነው) በጀት ዓመት፣የዳይሬክተሮች ቦርድ እና ማኔጅመንት፣ የጠቅላላ ታካፉል (ኢስላሚክ) ኢንሹራንስ ሽፋን በመጀመር፣ በውል ሥራ፣ በአደጋና ካሳ አስተዳደር፣ በሪስክ አስተዳደርን፤ እንዲሁም በአጠቃላይ በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ፣ ጥንቃቄ የተሞላበት፣ ውጤታማና ሙያን መሠረት ያደረገ የውል አሰጣጥ ሥርአት እንዲሰፍን የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን፡፡

በዋና ዋና ፋይናንሺያል ዕቅዶችን በተመለከተ፤ በያዝነው በጀት አመት አጠቃላይ አረቦን የሽያጭ መጠን ብር 1.2 ቢሊዮን ፣ የካሣ ክፍያ ብር 790 ሚሊዮን ፣ አስተዳደራዊ ወጪዎች ብር 229.8 ሚሊዮን ፣ አቅደን በመሥራት ላይ እንገኛለን፡፡ በዚህ ረገድ የሩብ ዓመቱ የአፈጻጸም ውጤት ተስፋ ሰጪ እንደሆነ አይተናል፡፡

ኩባንያችን እ.ኤ.አ እስከ 2031 ድረስ ከትላልቅ የግል መድህን ሰጪዎች ውስጥ አንዱና መሪ ለመሆን የነደፈውን ራዕይ ለማሳካትና የበለጠም ውጤት ለማስመዝገብ ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና ከማኔጅመንቱ ከፍተኛ የሆነ ጥረት ከመጠየቁም በላይ በተለይም የኩባንያው ባለአክሲዮኖች በዋናነት የኩባንያውን የካፒታል አቅም በማሳደግ እንዲሁም እንደተለመደው ያላሰለሰ ድጋፋችሁን ከምንግዜም በላይ አጠናክራችሁ እንድትሰጡን በአፅእኖት እንጠይቃለን፡፡

### 4.3. ኢንቨስትመንት፣

- የኩባንያው የኢንቨስትመንት ገቢ ለማጠናከር እና ዘላቂ የሆነ ትርፋማነትን ለማረጋገጥ አሁን ያለውን ውሱን ኢንቨስትመንት ማሻሻል ግድ ይላል፤ ይህንንም ለማሳካት የኩባንያውን የተከፈለ ካፒታል መጠን ማሳደግና የፋይናንስ አቅማችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን የ“Liquidity” ምጣኔ/’ስታንዳርድ’ ግምት ውስጥ በማስገባት አዋጪ በሆኑ የረጅምና አጭር ጊዜ ኢንቨስትመንቶች ላይ ተጨማሪ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት በማድረግ የተሻለ ገቢ ለማምጣት ጥረት ይደረጋል፡፡ ለዚህም መሳካት ውድ ባለአክሲዮኖች እንደተለመደው ያላሰለሰ ድጋፋችሁን ከምንግዜም በላይ አጠናክራችሁ እንድተሰጡን በአፅእኖት እንጠይቃለን፡፡

## 4.4. አይቲ ሲስተም፣

• የኦፕሬሽን እና የድጋፍ ሰጪ ሥራዎችን በማዘመን፣ ወጪን ለመቀነስ እና ውጤታማ ሲያደርግ የሚችል ቴክኖሎጅ እና የአሰራር ሲስተም በመጠቀም፣ የአገልግሎት አሠጣጥ ደረጃን ለማሳደግ እንዲቻል፣ ኩባንያው ከፍ ያለ መዋዕለ-ንዋይ በማፍሰስ የዘረጋውን የአይ.ቲ. ሲስተም አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል በትኩረት ይሠራል፡፡

## 4.5. ዓለም-አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት ሥርዓት (IFRS)፣

ሀገር ውስጥ ያሉ ማናቸውም የፋይናንስ ተቋማት ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርቶችን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት ሥርዓት (IFRS -4) መሠረት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ግዴታ ተጥሎ የነበረ በመሆኑ፤ ኩባንያችንም፤ በዚሁ መሠረት ይህንን ስታንዳርድ፣ ወይም የሪፖርት አዘገጃጀት ሥርዓት ተግባራዊ አድርጓል፤ በቀጣይም አሁን እየተገበረው ያለው IFRS -4 ን ፋይናንሻል ተቋማት በ IFRS 9 እና 17 እንዲተኩ በህግ በተጣለው ግዴታ መሠረት ተግባራዊ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

## 4.6. የተፈረመና የተከፈለ ካፒታል ማሣደግ፣

በአሁኑ ወቅት የኩባንያችን የተከፈለ ካፒታል መጠን ብር 288.1 ሚሊዮን የደረሰና አጠቃላይ የተፈረመ አክሲዮን መጠኑም ብር 300 ሚሊዮን የደረሰ ቢሆንም፤ የተከፈለ ካፒታል አቅማችን ኩባንያው አሁን ከደረሰበት የኦፕሬሽን ዕድገት ጋርና ከኢንዱስትሪው 'ስታንዳርድ" አንጻር ማሻሻል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

የካፒታል መጠናችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካወጣው ዝቅተኛ መስፈረት ብር 500 ሚሊዮንም ሆነ አሁን ኩባንያው እያስመዘበገ ካለው የአረቦን ገቢ እድገት አንፃር ሲታይ ካፒታሉን ማሳደግ የኩባንያውን ህልውና ለማቀጠል ወሳኝና ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፤ የተከፈለ ካፒታል ማሳደግ፤ ባንድ በኩል ብሔራዊ ባንክ የጣለውን ግዴታ ከሟሟላት አኳያ አስፈላጊ ሲሆን፤ በሌላ በኩል፤ የኩባንያውን አቅም በማጎለበት ከፍተኛ የዋስትና ኃላፊነት መጠንን (High Risk Sum Insured) ለመሸከም እንዲችል በማድረግ የኩባንያችንን ተወዳዳሪነት እና ተመራጭነት ዕድገትና የሚያጠናክር በመሆኑ፤ ጥቅሙ ለሁላችን ነው፡፡

በመጨረሻ ኩባንያው በቂ የሆነ የካፒታል አቅም ቢገነባ ቦርድና ማኔጅመቱ በኃላፊነት ስሜት ተንቀሳቅሰው ገንዘቡን አዋጪ ኢንቨስትመንት ላይ በማዋል የተሻለ አቅምና ጥቅም ለማስገኘት እንደሚጥሩ ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

## 6. ማህበራዊ ሀላፊነት (Corporate Social Responsibility)፣

አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ) የስራ እድሎችን ከመፍጠሩም ባሻገር በህግ የተጣለበትን ግብር በወቅቱ በመክፈል ለሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ለተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች የሚውል ድጋፍ በማድረግ እና የተለያዩ ማህበረሰብ አቀፍ እንቅስቃሴዎችን በመደገፍ የበኩሉን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡ ይህንንም ተግባር የበለጠ አጠናክሮ በመቀጠል የማህበረሰብ ሀላፊነቱን ይወጣል፡፡

**ውድ ባለአክሲዮኖች!**

በመጨረሻም፣ ኩባንያችን በበጀት ዓመቱ ባደረገው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ፣ አመርቂ ውጤት እንዲያገኝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ከጎናችን ለቆማችሁ የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች' ደንበኞች፣ የማኔጅመንት አባላት፣ አጠቃላይ የኩባንያው ሠራተኞች፣የጠለፋ ዋስትና ሰጪ ድርጅቶች፣ የመድን ሰጪዎች ማህበር፣ የኢንሹራንስ ብሮከሮች፣ የሽያጭ ወኪሎችና እንዲሁም የዘወትር ድጋፋቸው ሳልተለየን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ፤ የዲሬክተሮች ቦርድ ልባዊ ምስጋናውን ለማቅረብ ይወዳል፡፡

እናመሰግናለን!!

**አብርሃም ገብረአምላክ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ**
**ታህሳስ 20 ቀን 2016 ዓ.ም.**
**አዲስ አበባ**